# ኪርክ ዳግላስ ምዕት ዓመታቸውን አከበሩ

ዓለማየሁ ታዬ

አሜሪካዊው ታዋቂ የፊልም ተዋናይ ኪርክ ዳግላስ ምእት ዓመታቸውን በሎስ አንጀለስ ከተማ ቤቨርሊ ሂልስ ሆቴል አከበሩ።

አዛውንቱ ጡረተኛ ተዋናይ የሃሊውድ ታላላቅ ሰዎች በተገኙበት የልደት በአላቸውን ሲያከብሩ የበኩር ልጃቸውና የሙያ ባልደረባቸው ማይክል ዳግላስን ጨምሮ ሶስቱም ወንድ ልጆቻቸው መገኘታቸው ተነግሩዋል።

የልደት ክብረ በዓሉን በንግግር የከፈተው ማይክል ዳግላስ በህይወቴና በሙያዬ ለተከናወኑት አበይት ስኬቶች ተጠቃሽ ባለወሮታው አባቴ ኪርክ ዳግላስ ናቸው ሲል የገለጠ ሲሆን የእንጀራ እናቱን ወ/ሮ አን ዳግላስም የወላጅ አባቱ የቀኝ እጅና መልካም ሴት ናቸው ሲል ተናግሩዋል።

የኪርክ ዳግላስ የስልሳ አመት የትዳር ጉዋደኛወ/ሮ አን በበኩላቸው ባለቤታቸውን ጉዋደኛዬ እና ፍቅረኛዬ በማለት አወድሰዋል።

የፊልም ተዋናይና የማይክል ዳግላስ ባለቤት ካትሪን ዚታ ጆንስ ለልደት በአሉ የተዘጋጀውን ሻማ በማብራት መልካም ልደት ለርስዎ የሚለውን ዜማ መርታለች።

የደስታ መንፈስ ይታይባቸው የነበሩት ጎምቱው ተዋናይ በልደት በአሌ ላይ ማን ንግግር ያርግ በሚለው ሃሳብ ላይ ልጆቼ ምርጫ አካሂደው ማይክል ዳግላስን መርጠዋል ምክንያቱም እሱ ከሁሉ የበለጠ ገንዘብ ስለሚሰራ ነው ሲሉ ቀልደዋል።

በኪርክ ዳግላስ የልደት በአል ለታደሙ ሰዎች የተዘጋጁት አብዛኞቹ ማእዶች የፊልም ባለሙያው በሰሩባቸው ፊልሞች ርእስ የተሰየሙ ሲሆን የዳግላስ ቤተሰቦች የታደሙበት ማእድ ሎንሊ አር ዘ ብሬቭ በተሰኘው ፊልም መሰየሙ ተጠቁሙዋል።

ስቲቨን ስፒልበርግን ፤ ጄፍሪ ካትዚንበርግን ፤ አርተር ኮህን እና ጄፍ ካንውን ጨምሮ በርካታ የሃሊውድ ታላላቅ ሰዎች በተገኙበት በዚሁ የልደት በአል የፊልም ዳይሬክተሩ ስፒልበርግ ባደረገው ንግግር ካብዛኞቹ ታዋቂ ተዋንያን ጋር

ሰርቻለሁ በህይወቴ ያጋጠመኝ ታላቅ የፊልም ባለሙያ ግን ኪርክ ዳግላስ ናቸው ሲል አድናቆቱን ገልፅዋል።

በ 1946 ዓም የፊልም ሙያቸውን የጀመሩት ኪርክ ዳግላስ በሴንት ሎረንስ ዩኒቨርስቲ እና አሜሪካን አካዳሚ ኦፍ ድራማቲክ አርትስ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን ከዘጠና በላይ በሚሆኑ ፊልሞች መተወናቸው ይታወቃል።

ኪርክ ዳግላስ በተለይ ዘ ባድ ኤንድ ዘ ቢውትፉል ኤስ ኢን ዘ ሆል አውት ኦፍ ዘ ፓስት ፓዝ ኦፍ ግሎሪ እና ሰቨን ዴይስ ኢን ሜይ በተሰኙ ተወዳጅ ፊልሞች በዋና ተዋናይነት መተወናቸው ይታወሳል።